## ከ ኤችአይቪ ጋር በደንብ መኖር ይችላሉ

የ SAYFSM አገልግሎቶች መመሪያዎችን እና ተስፋን እንዲያገኙ ይረዱዎታል ። እነዚህ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች በ SAYFSM ለእርስዎ ተደራሽ ይሆናሉ

- በ ኤችአይቪ ለተያዙ አፍሪካውያን የስሜታዊ እና መንፈሳዊ ድጋፍ ቡድን
- የ ኤችአይቪ ምክር እና ምርመራ
- ኤችአይቪ፣ ኤድስንየመከላከል ትምህርት
- በ ኤችአይቪ ለተያዙ የሚሰጥ የመከላከል ጣልቃ ገብነት እና የጤና ትምህርት
- በባህል እና በቋንቋ የሚቆራኙ የትምህርት ቁሳቁሶች
- የሕክምና ጉዳይ አያያዝ
- የህክምና ተሟጋችነት • የአእምሮ ጤና ማማከር
- ለቤቶች ፣ ለቅጥር ፣ ለህዝብ ድጋፍ ፣ ለምግብ መደርደሪያ ፣ ለልብስ ፣ ለትምህርት ፣ ለህጋዊ ፣ ለቤት ቁሳቁሶች እና ለሌሎችም ፍላጎቶች የሚሆኑ ግብኣቶች እና ሪፈራል ።

## ይመርመሩ!

ሁሉም የምርመራ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በ SAYFSM ጽ/ቤት በነፃ የሚሰጡ ናቸው።

SAYFSM የደም ምርመራን የሚያከናውነው በደንብ በሰለጠኑ እና የምስክርነት ወረቀት ባላቸው ሰራተኞች የሚከናወነውን መደበኛ ፈጣን የ ኤችአይቪ ምርመራ ኪት / ኦራኪዊክ ኪት በመጠቀም ይሆናል ።



ቀጠሮ ለመያዝ ለ SAYFSM ይደውሉ እና የሠራተኛ አባላትን ጋር ይነጋገሩ።

የምርመራ ውጤቶች በ 15 ደቂቃዎች ውስጥ።

አድራሻችን:
SAYFSM
2395 University Avenue, #200,
St. Paul, MN 55114

ስልክ ቁጥራችን (651) 644-3983
ኢሜይል: info@sayfsm.org
ድረ ገፅ:www.sayfsm.org

### ነፃ የ ኤችአይቪ ምርመራ ጣቢያዎች

| | |
|---|---|
| SAYFSM | 651-644-3983 |
| Rainbow Health | 612-341-2060 |
| Red Door | 612-543-5555 |

ልገሳዎች በደስታ ይስተናገዳሉ!
አዎ! ለ SAYFSM ማበርከት እፈልጋለሁ:

____$25 ____$10 ___$5 ___ ሌላ

እባክዎ ልገሳዎን ለ:
SAYFSM
2395 University Avenue W, #200
St. Paul, MN 55114

እናመሰግናለን!!

ባህላዊ ተስማሚ የሆኑ አገልግሎቶችን ማቅረብ

በሚኔሶታ ውስጥ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ወጣቶች እና የቤተሰብ አገልግሎቶች (SAYFSM) ሚኔሶታ ውስጥ ላሉት አፍሪካውያን ሁሉ በባህላዊ ስሜት እና በቋንቋ ተስማሚ የ HIV/AIDS ትምህርት እና ማህበራዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል ።

# Mbiu

የ SAYFSM መፅሔት Issue 24/February 2023 የታተመ

651-644-3983 www.sayfsm.org info@sayfsm.org

# ስጦታም እርግማንም አይደለም



*ፓስተር ፍቅሩ ኢቲቻ*

ኤችአይቪ/ኤድስ ከአራት አስርት አመታት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም፣ ዳሰሳ እና ጥናቶች እንደሚያሳዩት ብዙ ሰዎች አሁንም የኤችአይቪ/ኤድስን መሰረታዊ እውነታዎች ሙሉ በሙሉ አልተረዱም።

ከእነዚህ መሠረታዊ እውነታዎች መካከል አንዳንዶቹ በኤችአይቪ እና በኤድስ መካከል ያለው ልዩነት፣ የኤችአይቪ መተላለፊያ መንገዶች፣ የኤችአይቪ መከላከያ እርምጃዎች እና በኤች አይ ቪ ለተያዙ ሰዎች የሚሰጠው ሕክምና እና እንክብካቤ ናቸው።

እንደነዚህ ያሉ መሰረታዊ የኤችአይቪ/ኤድስ እውነታዎችን አለመረዳት አንዳንድ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩትን ወደ ማግለልና መድሎ መምራቱ የማይቀር ነው። ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ለኤችአይቪ / ኤድስ ውጤታማ መድሃኒት ባይኖርም፤ ኤችአይቪ / ኤድስ የሞት ፍርድ አይደለም፡፡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ቀደም ሲል ለተያዙት የተለያዩ የእድሜ ማራዘሚያ መድሐኒቶችን እና እንክብካቤዎችን አምጥተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከኤችአይቪ ጋር የሚኖሩ ፣ ያለውን ህክምና እና እንክብካቤን የተከታተሉ ሰዎች ውጤታማ ህይወት እየመሩ ነው እና ሁሉም ሰው ያለውን የኑሮ እድል አላቸው። በተመሳሳይ ጊዜ የመከላከል እና የጉዳት ቅነሳ ግብአቶችም ቀርበዋል፡፡

በ2021 ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ወጣቶች እና ቤተሰብ አገልግሎቶች የማህበረሰብ አቀፍ የእውቀት ግምገማ መሰረት የኤችአይቪ/ኤድስ እውነታዎች ላይ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ግለሰቦች ኤችአይቪ የእግዚአብሄር እርግማን እንደሆነ እና ከኤችአይቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሰዎች በራሳቸው ማፈር አለባቸው ብለው ያምናሉ።

እንዲህ ያለው አለመግባባትና የተሳሳተ ግንዛቤ አንዳንድ ሰዎች ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩትን ሰዎች ወደ ማግለልና መድሎ መምራቱ የማይቀር ነው። ኤችአይቪ ለሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታም እርግማንም አይደለም፤ ነገር ግን የሰውን አካል በመበከል ኤድስ የሚባለውን በሽታ የሚያመጣ ቫይረስ ነው።

መገለልና መድልዎ ሁልጊዜም በኤችአይቪ /ኤድስ የሚኖሩ ሰዎች ወጥተው ልምዳቸውን ለሕዝብ እንዳያካፍሉ ያደርጋቸዋል። ስለ ኤችአይቪ ኢንፌክሽን ስናወራ ከኤችአይቪ ኢንፌክሽን ጋር በቅርበት የተገናኙ ሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖችን መርሳት የለብንም ። በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሌሎች በሽታዎች መኖር በኤችአይቪ በቀላሉ እንዲያዙ ሊያደርግ ይችላል እና በተገላቢጦሽም እንዲያው፡፡ ሁሉም ሰው የኤችአይቪ ምርመራ እንዲያደርግ እና ለሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ እንዲያደርግ ይበረታታል።

ስለ ኤችአይቪ/ኤድስ፣ ስለ መከላከያ መንገዶቹ እና በኤችአይቪ ለተያዙ ሰዎች ስለሚሰጠው ህክምና መሠረታዊ እውነታዎች በቂ መረጃ ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው። የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያ እና የእንክብካቤ ግብአቶችን ማግኘት የሚቻለው የመጀመሪያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችዎን፣ በዋነኛነት በኤችአይቪ/ኤድስ እና በተዛማጅ ኢንፌክሽኖች ላይ የሚሰሩ የአፍሪካ ማህበረሰብ አቀፍ ኤጀንሲዎችን፤ የጤና ትምህርት በንቃት እየሰጡ ያሉ በእምነት ላይ የተመሰረቱ ድርጅቶች እና የማህበረሰብ ማዕከላትን በመጠየቅ ነው።

ኤችአይቪ ን እንዋጋ -
ከ ኤችአይቪ ጋር የሚኖሩትን ሳይሆን

ሰዎች በ ኤችአይቪ የተያዙ እንደሆነ ማወቅ አይፈልጉም ፣ ምክንያቱም ቤተሰቦቻቸው እና ማህበረሰባቸው እንዳይፈርድባቸው እና እንዳያገሉዋቸው ስለሚፈሩ ነው ። ኤችአይቪ / ኤድስ ያለባቸው ቢሆንም እንኳ ሁሉም ሰው ሁልጊዜም እንደሚወደድ እና እንደሚደገፍ ማወቅ አለበት ።

ኤድስ ን የሚያስከትለው ቫይረስ በንክኪ ፣ በምራቅ ፣ በእንባ ፣ በማስነጠስ ፣ በሳል ወይም በማንኛውም ዓይነት ተራ የሆነ ንክኪ አይሰራጭም ። ኤችአይቪ በዋነኝነት የሚተላለፈው ኤችአይቪ ቫይረስ ካለበት ሰው የዘር ፈሳሽ ፣ የሴት ብልት ፈሳሽ ፣ የፊንጢጣ ፈሳሽ ፣ ደም ወይም የጡት ወተት ነው ።





## ስለ ኤችአይቪ መወቅ ያለብዎት ነገር ምንድን ነው?

### “እውቀት ከሀብት ይሻላል።” የካሜሩንያን አባባል

ኤችአይቪ / ኤድስ **ምንድን ነው?**

- ኤችአይቪ / ኤድስ ን የሚያስከትል ቫይረስ ነው ። ሰውነታችንንም ከበሽታዎች እና ኢንፌክሽኖች የሚከላከለው የሰውነት ተፈጥሯዊ የመከላከያ ዘዴ የሆነውን በሽታ የመከላከል ስርዓትን ይጎዳል ።
- በበሽታው ከተያዙ በኋላ፣ የበሽታ ምልክት ሳይኖርብዎት ወይም በ ኤችአይቪ መያዝዎን ባለማወቅ ለብዙ ዓመታት መኖር እና ለሌሎች ማስተላለፍ ይችላሉ ።
- ለዓመታት በ ኤችአይቪከተያዙ በኋላ በሽታ የመከላከል ስርዓትዎ በጣም ይጎዳል እናም ኢንፌክሽኑም ወደ ኤድስ ያድጋል ።
- ኤድስ ማለት የ ኤችአይቪ የመጨረሻ ደረጃ ነው ።
- ኤድስ ን ለይቶ ማወቅ የሚችለው ዶክተር ብቻ ነው ።
- ለ ኤችአይቪ / ኤድስ ምንም አይነት ክትባት ወይም መድኃኒት

የለም ።

- ምንም እንኳ የደህንነት እርምጃዎች ስራ ላይ ካልዋሉ ወይም መርፌ ያጋሩ እንደሆነ አሁንም ኤችአይቪን ወደ ሌሎች ሊያስተላልፉ ቢችሉም፤ በ ኤችአይቪ የተያዙ ብዙ ሰዎች ጤናማ እና ረጅም ህይወት እንዲኖሩ ለመርዳት ህክምና ይሰጣል ።
- ከህክምናዎቹ ተጠቃሚ ለመሆን ቀደም ብለው የ ኤችአይቪ ውጤትዎን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው ። የ ኤችአይቪ ውጤትዎን ማወቅ የሚችሉት የ ኤችአይቪ ምርመራ በማድረግ ብቻ ነው።

ኤችአይቪ አይለይም!
ማንኛውም ሰው በ ኤችአይቪ ሊያዝ ይችላል!